የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

# ዜና መፅሔት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 72 ጥር 2018 ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

ዌብሳይት:- http:www.eaa.gov.et

ፌስቡክ:- Ethiopian Agricultural Authority

ቴሌግራም:-eaapr_1234

## ባለስልጣኑ የውል ስምምነት ተፈራረመ







ባለስልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ጥራትና ደህንነታቸውን የማረጋገጥ የቁጥጥር ሰራ ይሰራል።

የኢትዮጵያን የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ከ186 የአለም ሀገራት ጋር በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማቀላጠፍ የሚያስችል ዲጂታል የኤሌክትሮኒክ ስረዓት ፋይቶሳኒተሪ ሲስተም (Electronic phytosanitary certificate ) ለአገልግሎት ዝግጁ በመሆኑ በአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በጋራ ለመስራት በዛሬው ዕለት ተፈራርሟል።

ባለስልጣኑ በኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ላይ ለባለሙያዎች ስልጠና ሰጠ።









የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከኢኖቬሽን ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር እና ከፔራጎ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ለእንስሳት መኖ ሪጉላቶሪ ባለሙያዎች ስልጠና ሰጠ።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ፣ እዉቅና ያለው እና መልካም ስም ያለው ተቋም እንዲሆን አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ በማድረግ ምቹ ፣ ቀልጣፋና ግልፅነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱ ተገለፀ።

ባለስልጣኑ ሁሉንም አገልግሎቶች ዲጂታላይዝ ያደረገ ሲሆን 29 የሚሆኑ አገልገሎቶችን ደግሞ በመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት አካቶ እየሰራ መሆኑ ተገልጿል።

ባለስልጣኑ በተለያዩ ጊዜያት የባለሙያዎችን አቅም በስልጠና በመገንባት የሪጉላቶሪ ስራው እንዲሳለጥና ምቹና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት እንዲሰፋን ከፍተኛ ስራ እየሰራ ይገኛል።

በባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ዘላለም አበበ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችን በኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ላይ ያላቸውን አቅም በመገንባት የአገልግሎት አድማሳችንን ለማስፋት ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል።

ባለሙያዎች በስልጠናዉ በቂ ግንዛቤ እንዳገኙና እራሳቸውን ከዲጂታላይዜሽን ሲስተም ጋር በማዋሀድ ለቀጣይ ስራቸው ምቹና ቀላል የአሰራር ሲስተም እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል።





PAGE 3

ማነኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕፅዋት፣የዕፅዋት ውጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ሳያገኙ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት አይችሉም፡-ባለስልጣኑ







በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የዕፅዋት ኳራንታይንና ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ መቅደስ ነጋ፣ የስራ ክፍላቸው ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩና እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕፀዋት ፣ የዕፅዋት ውጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ በመስፈርቱ መሰረት ቁጥጥር እንደሚያደረግ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ውስጥ በዋናነት የቡና ምርት፣ የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ እህል፣ የአበባ ምርት፣ አትክልት፣ ቅመማ ቅመሞች እና ልሎች ምርቶች ወደ ተለያዩ አህጉራት ማለትም ኤሽያ፣ አውሮፓ፣አሜሪካ፣ አፍሪካ፣ አውስትራሊያ እና አረብ ሀገሮች እንደምትልክ ተናግረዋል።

ባለስልጣኑ የዕፅዋትና አዝዕርት ድንጋጌ ቁጥር 56/1971 ፣የዕፅዋት ኳራንታይን ደንብ ቁጥር 4/1992፣ ማንዋሎችና የአለም አቀፍ መስፈርቶችን/ISPMs/ መሰረት በማድረግ በባለስልጣኑ በመውጫና መግቢያ በጣቢያዎች ላይ የሰነድ ፍተሻ፣ ምርቱ ባለበት ቦታ በመገኘት የእይታ ፍተሻ በማድረግ እንዲሁም የተባይ ክስተት ጥርጣሬ ሲኖር ወካይ ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ማሟላቱን በማረጋገጥ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር እንዲላክና በተመሳሳይም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ፈቃድ እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

የስራ ክፍሉ ከሰራቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የአለም አቀፍ የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት/IPPC/ ባወጣው የፈራሚ ሀገራት አሰራራቸውን የሚፈትሹበት መስፈርት (Phytosanitary Capacity Evaluation/PCE/ Tool) በተቀመጠው 13 ሞጁል/Modules/ ከሚመለከታቸው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት(የስራ ሀላፊዎች ፣ ተመራማሪዎች፣ ዩንቨርስቲዎች፣ማህበራቶች፣ተቆጣጣሪ መንግስታዊ ተቋማት፣ላኪዎች፣ አስመጪዎች )እና ሌሎች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ብሕራዊ ዕፅዋት ጥበቃ ድርጅት/ET NPPO/ በተገኙበት ፍተሻ መደረጉን ገልጸዋል።

በተደረገዉ ፍተሻም ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሀገራት የተሻለ አፈጻጸም እንዳላት ገልጸው፤ ያሉትን ክፍተቶች በመለየትና ክፍተቶቹን ለመሙላት የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ መዘጋጀቱንም አብራርተዋል። ወደ ገፅ 4 ዞሯል

**ከገፅ 3 የዞረ**

ኢትዮጵያ የዕፅዋት ውጤቶችን ወደ ውጭ ለመላክ በየአመቱ Xylella fastidiosa ባክቴሪያ ነጻ መሆኗን ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባታል ብለው፤ በዚህም መሰረት Xylella fastidiosa የተባለ የዕፅዋት ባክቴሪያ ከእርሻዎች እና ከሌሎች አካባቢ የዕፅዋት ናሙና በመውሰድ በሆለታ ብሄራዊ የባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማዕከል የላብራቶሪ ምርመራ በማድረግ ኢትዮጵያ ከባክቴሪያው ነፃ እንደሆነች ሪፖርት ለሚመለከተው አካል መላኩንም ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ወደ አውሮፓ በሚላኩ የአበባ ምርቶች ላይ በአውሮፓ ህብረት ኦዲተሮች እና ወደ አሜሪካ በሚላኩ የአበባ ቁርጥራጮች/Pelargonium/Cuttings/ በአሜሪካ ኦዲተሮች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዕፅዋት ጥበቃ ድርጅት/ NPPO/ ኦዲት እንደተደረገች ገልጸዋል፡፡


ወደ ውጭ ለሚላኩ ምርቶች የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ደግሞ የቅደመ ማስገቢያ ፈቃድ እና ከገባ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂ ፈቃድ ለመስጠት ሶስቱን አንድ ላይ ያጣመረ ኢፋይቶ ሶሉሽን (ePhyto Solution) ዲጅታል ስረዓት መዘርጋቱን እና አሰራሩም ከአፍሪካ ሀገራት የተሻለ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የጣቢያ ኢንስፔክተሮች ወደ ሀገር በሚገቡ እና በሚወጡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶችን በተመለከተ የዕፅዋት ድንጋጌ 56/1971 ፣የዕፅዋት ኳራንታይን ደንብ ቁጥር 4/1992 ፣ የዕፅዋት ኳራንታይን የአሰራር ማንዋሎችና የአለም አቀፍ መስፈርቶችን/ISPMs/ መሰረት በማድረግ የፍተሻና የቁጥጥር ስራዎች እንደሚሰሩ እና ማነኛውም ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ከባለሥልጣኑ የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ሳያገኙ ወደሀገር ውስጥ መግባት እንደማይችሉ አስረድተዋል ፡፡

በቁጥጥር ስርዓቱ መስፈርቱን ያላሟሉ እንዲሁም ኳራንታይን ተባይ የተገኘበት ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁስ ላይ በፋይቶ ሳኒታሪ እርምጃዎች መሰረት የማንጻት ፣ ወደመጣበት ሀገር የመመለስ እና እንዲወገድ የማድረግ እርምጃ እንደሚወሰድም ተናግረዋል፡፡

በዚህ የበጀት ዓመት ውስጥ የተካሄደው የከፍተኛ ደረጃ የክልል SPS ኮንፈረንስ በመክፈቻ ንግግሮች፣ መልዕክቶች፣ የቀረቡ የተለያዩ ሰነዶች፣ የፓናል ውይይቶች እና የእውቅና ሽልማት መድረኮች በአጠቃላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳዩ መድረኮች ሆነው መቅረባቸውን ተናግረዋል፡፡

በስራ ክፍሉ እና በባለሥልጣኑ በሚሰጡት አገልግሎቶች ላይ ከአፍሪካ፣ አውሮፓ፣ ከተለያዩ ኢንባሲዎች የመጡ ተወካዮች፣ ከክልል ተቆጣጣሪ አካላት፣ ከባለድርሻ እና ከንግድ አካላት (አስመጪዎች፣ ላኪዎች)፣ ማህበራት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማበረታት ትልቅ እና አስፈላጊ መድረኮች እንደነበሩ ጠቅሰው በተጨማሪም መድረኩ አብሮ መስራት፣ መተባበር፣ መቀናጀት እና የተለያዩ ልምዶችን ለመማር በአህጉራዊ እና በዓለምዓቀፋዊ ደረጃ ትብብርን ለማሳደግ እና አቅምን ለማጎልበት ዋና ቁልፍ መድረክ መሆኑን ወ/ሮ መቅደስ ገልጸዋል፡፡









# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ አንደኛ በመውጣት እውቅና ተሰጥቶታል





የዘንድሮው አካቶ ትግብራ ከተመዘገቡ 22 ተቋማት ውስጥ 6 ቱ መስፈርቱን ባያመሟሉም 16ቱ ግን ዝቅተኛውን መስፈርት እንኳን ማመሟላት እንዳልቻሉ የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የሴቶች ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው በአካቶ ትግበራ አፈፃፀም ምዘና ላይ ተሳትፈው አንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃ ይዘው ባጠናቀቁ ተቋማት ባዘጋጀው የእውቅና መርሀ ግብር ሲሆን ሀላፊነታቸውን የማይወጡ ተቋማት ላይ ተጠያቂነት እንደሚፈጥር ተገልጿል።

የሴቶች የአካል ጉዳተኞች፣ የአረጋዊያንና ሌሎች ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ በዚህ የአካቶ ትግበራ አፈፃፀም ላይ የምክክር መድረክ ያካሄደ ሲሆን

በመድረኩም የሴቶች አካል ጉዳተኞች ፣ አረጋዊያንና ሌሎች ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ በዚህ የአካቶ ትግበራ አፈፃፀም የምዝና ሂደት የግብርና ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር የተሻለ ውጤት የነበራቸው ነው የተባለው ሆኖም ግን የእነዚህ የሁለቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ተጠሪ በሆኑ 22 ተቋማት ማለትም 13 የጤና ሚኒስቴር እና 9 የግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት ውስጥ በዚህ ዓመት በተካሄደው የአካቶ ትግበራ አፈፃፀም ምዘና አብዛኛዎቹ ዝቅተኛውን መስፈርት እንኳን ማሟላት እንዳልቻሉ ተነግሯል።

በዚኅም መሰረት ከግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስጣን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ አንደኛ በመውጣት እውቅና ተሰጥቶታል።



# ባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒት አስተዛዘዝ መመሪያን ለባለድርሻ አካለት ይፋ አደረገ።




የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከFSRP ጋር በመተባበር የክልል የእንስሳት ምርትና ግብዓት ተቆጣጣሪዎች ፣የባለስልጣኑ የአራቱም ማዕከል ሀላፊዎች እና ሌሎች ባለድረሻ አካላት በተገኙበት የያዘጋጀውን እንስሳት መድኃኒት አስተዛዘዝ መመሪያን አስተዋውቋል።

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት መድኃኒት ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ሰለሞን ከበደ(ዶክተር) ለስራው የሚስፈልጉ የአሰራር አዋጆች፣ መመሪያዎች እና ቴክኒካል ጋይድላይኖች በስፋት መዘጋጀታቸውን ገልፀዋል።

ከተዘጋጁት መመሪያዎችና ጋይድላይኖች መካከል በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1022/2016ን ለመድረኩ ገለፃ አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የእንስሳት መድሃኒት አስተዛዘዝ መመሪያ እንደ ሞዴል መዘጋጀቱንም አስረድተዋል ።

ክልሎች የፀደቀውን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉት እና እንደ ሞዴል የተዘጋጀውን መመሪያ መሰረት አድርገው ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዘጋጀተው ስራ ላይ እንዲያውሉት በመድረኩ አሳስበዋል ።

ህገ-ወጥ የእንስሳት መድሃኒትን ለመቀነስ፣ አግባበዊ የሆነ የእንስሳት መድሃኒት አጓጓዝ፣ አከመቻቸት እና አጠቃቀም እንዲኖር በማድረግ የመድሃኒት ጥራት መጓደልን እና አላግባብ አጠቃቀምን ለመቀነስ የተዘጋጀው መመሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ የእንስሳት ሀኪሞች ማህበር ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር እንድሪያስ ዘውዴ የመመሪያው መዘጋጀት የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲሻሻል፣ አርብቶና አርሶ አደሩ ተጠቃሚ ሆነው ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኜት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እንዲታገኝ አስተዋፅኦ ያደረጋል ብለዋል።


መመሪያው የባለሙያው አቅም ከፍ የሚያደርግና እና የእንስሳት መድኃኒት አስተዛዘዝና አጠቃቀም ላይ ሙያዊ ሀላፊነታቸውን እንድወጡ ያደርጋል ሲሉ ገልፀዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው ህገወጥ የእንስሳት መድኃኒት ዝውውርን ለመቀነስ ፣በእንስሳት መድኃኒት አስተዛዘዝና አጠቃቀም ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከባለስልጣኑ ጋር በቅንጅት እንደሚሰሩ በመደረኩ ተናገረዋል።

PAGE 7

## ባለስልጣኑ ወቅታዊ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስራን በሚመለከት ከባለድርሻ አካላት ጋር የዉይይት መድረክ አካሄደ::






ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በክልል ከሚገኙ የእጽዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ወቅታዊ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስራን በሚመለከት በበይነ መረብ በመታገዝ በኦላይን የመጀመሪያውን ሳምታዊ ቨርቹዋል ሚቲንግ / Virtual meeting/ በትላንትናው ከጠዋቱ 2፡00 ጀምሮ አካሄደ::

የዉዉይይትመድረኩዋናዓላማከተቆጣጣሪአካላት ጋር በመተጋገዝ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን በትብብር ለመስራት፣ የስራ ግንኙነትን ለማጎልበት መረጃን በቀላሉ ለመለዋወጥና፣ ለ ሚያጋጥሙ ችግሮችና ማነቆዎች በጋራ በመወያየት መፍትሔዎችን ለማስቀመጥ እንደሚያግዝ የውይይቱ ሰብሳቢ የዕፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ወንዳለ ሀብታሙ አስረድተዋል።

የዕፅዋት ዝርያ ዘር ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ፍሰሀ ተሾመ ፤ የሬጉላቶሪ ተቋም ካቋቋሙ ክልሎች የተላኩትን ሳምንታዊ መረጃዎች ውስጥ ምን ያክል አዲስ እና የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ እንደተሰጠ ፣የየክልሉ የዘር ኢንስፔክሽን አፈጻጸም ሪፖርት እና ያደረ ዘር የጥራት ቁጥጥር የተደረሰበትን መረጃ በዝርዝር ለተሳታፊዎች አቅርበዋል።

የዕፅዋት ዝርያ ዘር ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ፍሰሀ ተሾመ ፤ የሬጉላቶሪ ተቋም ካቋቋሙ ክልሎች የተላኩትን ሳምንታዊ መረጃዎች ውስጥ ምን ያክል አዲስ እና የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ እንደተሰጠ ፣የየክልሉ የዘር ኢንስፔክሽን አፈጻጸም ሪፖርት እና ያደረ ዘር የጥራት ቁጥጥር የተደረሰበትን መረጃ በዝርዝር ለተሳታፊዎች አቅርበዋል።

አቶ ፍሰሀ አክለዉም የቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከር ባለስልጣን መስሪያቤቱ የአቅም ግንባታ ስራዎችን፣ የዲጂታል ስራዎችን እና የህግ ማዕቀፍ ስራዎች እንዲጠናቀቁ በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በልዩ ሁኔታ መታገዝ ያለባቸውን ጀማሪ የተቆጣጣሪ ተቋማት ለማጠናከር እንደሚሰራም ተናግረዋል ፡፡

ክልሎችም የቀረበው ሪፖርት በላኩት መረጃ መሰረት መሆኑን ገልጸው ተጨማሪ ማብራሪያና ገለጻ የሰጡ ሲሆን በቀጣይ ሳምንት ውስጥ ተጨማሪና ግብዓት ይሆናል የሚሉትን መረጃ አካተው እንደሚልኩ ገልፀዉ ፤ የውይይት መድረኩ ለስራቸው መሳካት እጅጉን ጠቃሚ መሆኑን በመናገር ባለስልጣን መስሪያቤቱ ይህንን በማድረጉ አመስግነዋል።በመጨረሻም ውይይቱ እንዲዳብርና እና የሬጉላቶሪው ዘርፍ እንዲጠናከር ሁሉም ክልሎች መረጃን በማጥራትና ከክልል ግብርና ቢሮዎች ጋር በመናበብ እንዲልክ የከረመውን ዘር በድጋሜ በመፈተሽ መልሶ በማሸግ አስፈላጊውን የቁጥጥር ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል ፣ በመሰፈርቱ መሰረት የወደቀውን ዘር በጥንቃቄ መረጃውን በመያዝ በአሰራር መመሪያው መሰረት እንዲወገድ ማድረግ፤ ለአዳዲስ የዘር ጥራት ማዕከላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ማዘጋጀትበየደረጃው ያለው የግብርና መዋቅር ለሬጉላቶሪው ዘርፍ ጠንካራ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማድረግ ፣ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ላይ ተገልጋዮች አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላታቸው ጥብቅ ክትል እንዲደረግ፣ በየጊዜው የኢዲትንግ ስራ እንዲከናወን ከቀሩት ክልሎች እና ከሁለቱ መስተዳደሮች (ድሬደዋና አዲስ አበባ) የሚመለከተው አካል እንዲሳተፉ እናእየተሰራበት ያለውን የዲጂታል ስራ በተለይም የባር ኮድ አጠቃቀም እና በአዲስ መልኩም ለመተግበር ጅማሮ ላይ ያለውን ዲጂታል የመለያ **ወደ ገፅ 8 ዞሯል**

**ከገፅ 7 የዞረ**

ምልክት ስራ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ማከናወን የሚሉ ቁልፍ ተግባራት እንዲከናወኑ ዉይይቱን የመሩት ዶክተር ወንዳለ ሀብታሙ አሳስበዋል።

**የእንስሳት መድኃኒት በተህዋስያን መለመድ ማለት ምን ማለት ነው?**

መድኃኒት በተህዋስያን መለመድ፡- ማለት ባክቴሪያ ወይም ቫይረስ ወይም ፈንገስ ወይም ጥገኛ ተህዋስያን በሽታ ሲፈጥሩ እና በሽታውን ለማከም የሚሰጠው መድኃኒት ምላሽ መስጠት ሲያቆም ወይም ሲቀንስ ለበሽታ መስፋፋት እና ለሞት ተጋላጭነትን ሲጨምር ነው።በአሁኑ ጊዜ የመድኃኒት በተህዋስያን መለመድ (Anti- Microbial Resistance) አገራችንን ጨምሮ በዓለም ላይ ለእንስሳትና የሰው ጤና እንዲሁም ለአካባቢ ደህንነት እንደስጋት ከሚቆጠሩ ጉዳዮች መካከል በዋናነት ይጠቀሳል።መድኃኒት በተህዋስያን መለመድ መንስኤ ተህዋስያ መድኃኒትን የሚላመዱበት መንገዶች:- ሀ. ውስጣዊ (የተፈጥሮ ሂደት)

ጀርሞች ወይም ተህዋስያን ራሳቸውን ከመድኃኒት ለመከላከል ተፈጥሮአዊ ለውጥ በማድረግ፣

ለ. ውጫዊ መንስኤ፡- በሚከተሉት ተግባራት ምክንያት ውጫዊ መንገዶች የመድኃኒት መላመድ ይከሰታል:- ያልተሟላ የሕክምና ዑደት፣በእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ሳይታዘዙ መድኃኒቶችን መጠቀም፣መድኃኒትን አላግባብ መጠቀም ወይም ከልክ በላይ መጠቀም፣የንፁህ ውሃ እጥረት እና የንፅህና አጠባበቅ ችግር፣ በቂ ያልሆነ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር፣ የመድኃኒት በጀርሞች በተህዋስያን መለመድ ላይ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የእውቀት ማነስ ማነስ በቃ ስልጠና እጥረት፣

**የመድኃኒት በጀርሞች በተህዋስያን መለመድ የሚያስከትለው ጉዳት**

የመድኃኒት በጀርሞች በተህዋስያን መለመድ ተጽዕኖ ብሄራዊ እና አለም አቀፋዊ ነው። እንደ የአለም ጤና ድርጅት(WHO) መረጃ መሰረት የመድኃኒት በጀርሞች በተህዋስያን መለመድ በአለም ላይ ካሉት 10 ቀዳሚ የጤና ስጋቶች አንዱ ነው። ከሚያስከትሉት ተፅዕኖዎች ውስጥ:- በሽታን እና ሞትን ይጨምራል፤ የጤና እንክብካቤ ወጪዎችን ይጨምራል፤ የመድኃኒት ጎጂ ባህሪያትን ይጨምራል፤ የእንስሳትን ደህንነት መጓደል ያመጣል፤

**የመድኃኒት በጀርሞች በተህዋስያን መለመድ መከላከያ መንገዶች**


የእንስሳት ባለቤቶች በባለሙያዎች የታዘዙ እና ህጋዊ መድሃኃኒቶችን ብቻ መጠቀም እና ከባለሙያ የተሰጣቸውን መመሪያዎችን በትክክል መከተል፤ የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ እና ተሳትፎ ማሳደግ፤ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የመድኃኒት በጀርሞች መለመድን ለመከላከል ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፤ አግባባዊ ያልሆነ የመድኃኒት አጠቃቀምን ማስወገድ፤ በእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም የተዘጋጁ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና የአተገባበር ማኑዋሎች በትክክል ስራ ላይ ማዋል፤ምንጫቸው ያልታወቀ የእንስሳት መድሃኃኒቶችን ለእንስሳት ህክምና አለመጠቀም፤ የእንስሳት ጤና አገልግሎት በላብራቶሪ የምርመራ ውጤት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፤ የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህናን መጠበቅ፤ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ለማድረግ ክትትል እና ምርምርን ማጠናከር፤ መልካም የመድኃኒት አጠቃቀም ልምዶችን ማዳበር፤




# ቡሬ ሴሣሡፓ

## አዝናኝና አስተማሪ ቀልዶች





ጴጥሮሴ ሆይ ጎራዴህን ካፎት ክተት
ኃይልህ አይሁን፣ ሰይፍ ጉልበት
ይልቅ ፍቅርን ልበስና
ወይ ከጌታህ ተዋስና
እንድትገሰው ላንዴ ባንዴ
ሰይፍ ሳይሆን ጦር ጎራዴ
ለዘመቻህ ፍቅርን ምረጥ
ጆሮ ሳይሆን ልብ እንዲቆርጥ።

## የታላላቅ ሰዎች አባባል

"አመስጋኝ ሰው በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ ያመሰግናል።

ባሁላህ

"ሕይወታችን መልካም ከሆነ፣ ጊዜው መልካም ይሆናል። ዘመናትን የምንሠራው እኛ ነን። ዘመናችን እኛን ይመስላል።"

ቅዱስ አውጉስቲን

"ንዴትን ማመቅ፣ በሰው ላይ ልትወረውረው ያሰብከውን ፍም በእጅህ ላይ እንደማቆየት ነው። የምትቃጠለው አንተ ነህ።"

ጓተማ ቡድሃ

"የሚሰጥህ በሠራኸው ሥራ ወይም በቆየህበት ጊዜ መጠን አይደለም። በፍቅርህ ልክ ነው።"

ቅድስት ካትሪን

አቡነ ሺኖዳ

